# የፕሬስ ነፃነትን በታዛነት መጠቀም እስከ መቼ?

**መስፍን ኃይሌ**

07/29/14

ሁሉንም ወገን የሚያግባባ ጉዳይ ነው - ሚዲያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በመገንባትና ብሔራዊ መግባባትን በመፍጠር ረገድ ጉልህ ሚና የሚጫወት ትልቅ መሣሪያ ስለመሆኑ፡፡ ሚዲያ ለበጎ ተግባር ከዋለ አገር አነቃንቆ ብዙ ለውጥ ማምጣት ያስችላል፤ በተቃራኒው ሥራ ላይ የሚውል ከሆነ ደግሞ ደም ያፋስሳል፣ ሕዝብ ያጫርሳል፣ አገር ያምሳል፡፡

በበለፀጉትም ሆነ ባዳጊ አገራት ውስጥ ዴሞክራሲን ለመተግበር ተነሳሽነቱን ያላቸው ዜጎች በተናጠል ይሁን አሊያም በቡድን ተደራጅተው ይህንን ታላቅ ተግባር ለመፈፀም ገና ሲያስቡ ቀድሞ የሚታያቸው ጉዳይ የዴሞክራሲያዊ ተቋማት የመኖር ሁኔታ ነው፡፡

ይህንን ለመከወንም ዜጎቹ የሚኖሩባቸው አገራት ዴሞክራሲያዊ ባህል ያላቸውን ግለሰቦች በተደራጀ አኳኋን ለማሰማራት የሚያስችሉ ዴሞክራሲያዊ ተቋሟት እንዲኖራቸውም ተግተው ይሰራሉ፡፡ ከእነዚህ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት መካከል ወሣኙ ሚዲያ ነው።

ሆኖም በማንኛውም አገር የሚገነባው ሚዲያ ከዚያ አገር ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ራሱን እየቃኘ እንጂ የበለፀገውን አሊያም የምዕራቡን ዓለም አሠራር እንዳለ ገልብጦ አይደለም፡፡ በግልጽ እንደሚታወቀው የምዕራቡ ዓለም ሚዲያ አራተኛው የመንግሥት መዋቅር ሆኖ ተግባሩን ያለከልካይ ሊከውን ይችላል።

በየሚዲያዎቹም ተራውን ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ሹማምንቱን ጭምር ብሎም በአገሪቱ ያሉ ገዥ ሆነ ተቃዋሚ ፖርቲዎችን የሚቃወሙ አሊያም የሚደግፉ ዘገባዎች ሊቀርቡበት ይችላሉ። ይሁንና እዚህ ላይ መታለፍ የሌለበት ትልቁ ቁም ነገር ቢኖር

ዘገባዎቹ የሚያጠነጥኑት የኒዮ ሊበራል ሥርዓቱን ዘላቂነት በሚያስቀጥል ሁኔታ ተደርሰው የሚዘጋጁ መሆናቸውን ነው።

በመሆኑም የኒዮ ሊበራል ሥርዓቱን አንቋሽሾ ወይም አጣጥሎና አናንቆ የሚሰናዱ ማናቸውም ዘገባዎች ቦታ አያገኙም፤ የሚዲያ ውጤቶቹም ጨርሶውኑ አያስተናግዷቸውም፡፡

ይህንን ጉዳይ በቀጥታ ከአገራችን ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አያይዘን እስቲ እንመልከት፤ በግል ፕሬስ ስም ተመዝግበው ፈቃድ የወሰዱ አንዳንድ አመፅ አታሚ ጋዜጦችና መፅሔቶች በምዕራቡ ዓለም ውስጥ ያለው ሚዲያ ከሦስቱ መንግሥታዊ መዋቅሮች ቀጥሎ ጠንካራውና ጡንቸኛው አራተኛው "ተቆጣጣሪ" የመንግሥት አካል ተደርጎ ስለሚወሰድ ኢትዮጵያ ውስጥም በዚህ መልኩ ግንዛቤው ተይዞ መሥራት ይገባናል በሚል ህሳቤ የምዕራቡን ዓለም ጋዜጠኝነት እንዳለ በግልባጭ ካልተቀበልን ሞታችን ዛሬውኑ ይሁን  እስከማለት የደረሱ አስመስሎባቸዋል፡፡

ስለ እውነት እንነጋገር ከተባለ ኢትዮጵያ ውስጥ የፕሬስ ነጻነት በአዋጅ ከተረጋገጠ ሁለት አሥርተ ዓመታት ብዙም ያልዘለለ እድሜ ቢኖረው ነው፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ የሚዲያው እድገት ከአገሪቱ አጠቃላይ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ጋር አብሮ እየጎለበተና እየዳበረ እንደሚሄድም የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡

ዛሬ ከምንም ነገር ተነስተን ሃያ አንድ ዓመታት ሊያስቆጥር የቻለውን የሚዲያ ነጻነታችንን፤  ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ የዳበረ ሚዲያ ካላቸው አገራት ጋር ስለምን በእኩል ደረጃ ሊሰለፍ አልቻለም ብሎ አጉል መሞገት ያስገምት እንደሆን እንጂ የሚፈይደው አንዳች ነገር የለም፡፡

ንጽጽሩም ቢሆን ምንን ከምንድነው? የሚለውን በጥሞና ማገናዘብ ጠቃሚ ይሆናል - እንዲህ አልን፣ እንዲህ ተናገርን ለማለት ካልሆነ በቀር፤ የግድ አፍ አስከፍቶ በመጋት ከአቅም በላይ ለማዋጥ መታተር ያህልን ያስቀጥራልና፡፡ ማንም እንደሚያውቀው የኢትዮጵያ የነጻ ፕሬስ ታሪክ አጭር ዕድሜ ያለው ነው፡፡ ሚዲያው ከአገሪቱ ሶሽዮ ኢኮኖሚ ጋር አብሮ በሂደት እየተገነባ የሚሄድ ተቋምም ነው፡፡ የሥርዓቱ  ነፀብራቅ

ነውና፤ ከዚያ በተጻራሪ በቀጥታ የምዕራቡ ዓለም ግልባጭ መሆን ይኖርብናል ብሎ መንጠራራት ደግሞ አጉል ልፋት ይሆናል፡፡ ለዚህም ምክንያት አለው፡፡

የምዕራቡ ዓለም በሚከተለው የኒዮ ሊበራል ሥርዓት ውስጥ ልማታዊ ዴሞክራሲ ሚዲያን ለመገንባት የሚቻልበት እድል እንደሌለ ሁሉ በልማታዊ ዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥም የኒዮ ሊበራሊዝም አቀንቃኝ ሚዲያን ለመፍጠር የሚያስችለው ምህዳር ለጊዜውም ቢሆን በሩ ዝግ ነው፤ አሠራራቸው፣ ግብና ዓላማቸው ለየቅል ነውና።

የዚህ ጽሁፍ ማጠንጠኛ የሆነው በዚያን ሰሞን ለንባብ የበቁት አንዳንድ የህትመት ውጤቶች ቀደም ሲል ካነሳሳሁት እውነታ ጭራሽ አፈንግጦ ብዙም በእውቀት ላይ የተመሠረተ ትንታኔና ማብራሪያ ሳያቀርብበት እንዲያው "ሾላ በድፍኑ" እንዲሉ የምዕራቡን ዓለም የሚዲያ ፍልስፍናን ሊያቃምሱን በማስገደድ - የሚያዘጋጇቸው መጣጥፎች ቢደንቁኝ ነው፡፡

የጽሁፉ ባለቤቶች ማምንት ቆጥረው ብቅ በሚሉት ጋዜጦች ላይ ቋሚ አምደኞች ናቸው፡፡ እነዚህ ቋሚ አምደኞች ዘወትር በብዕራቸው የሚተፏቸው ተስፋ ማጣትን፣ ጨለምተኝነትን፣ ክስረትን ነው፤ በጎ ማሰብ ርቋቸዋል፤ ብርሃን አይታያቸውም፤ በጋዜጣዎቹና መጽሄቶቹ ላይም ይህንኑ ተዘውታሪ የጥፋት፣ የውድቀት፣ የሰቆቃ ጩኸታቸውን አላቋረጡም፡፡

የሽብር እምቢልታቸውን ለመንፋት አልቦዘኑም፤ ይህንንም አድርገውታል፡፡ በጎና መልካም ሁኔታዎችን ለማብጠልጠል ያው በሽንቋጭ ተዘውታሪ ብዕራቸው መንግሥትን ማጠቋቆሩን፣ ማጠልሸቱን፣ ጭቃ መቀባባቱን፣ ማጣጣሉን ቀጥለውበታል፤ የተለመደ ተግባራቸውን በብዕራቸው ገፉበት ሊባል ካልሆነ በቀር ምንም አዲስ የሚገልፁልን ጉዳይ የለም፡፡ በእርግጥ በዚህ ሰሞኑ መጣጥፋቸውም ሳት ብሏቸው ሳይሆን አይቀርም ከወትሮው በመለየት ሐቀኛና በእውቀት ላይ የተመሠረተ አስተያየት ሰጪ ለመምሰል ለአንዳንድ ነጥቦች ዋቢ ለማጣቀስ ዳድቷቸዋል፡፡ ቀዝቃዛውን የዓለም ጦርነት ማክተም ተከትሎ ብቅ...ብቅ ማለት የጀመሩ መንግሥታት ኢሕአዴግንም ይጨምራል በነፃ ኘሬስና የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን በመከተል በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማበብ እንደሚታወቁ ያገጠጠ ሀቅ ነውና በመጣጥፋቸውም ሊክዱቸው አልደፈሩም፤ ለዚህ

ሀሳብ ማጎልበቻ እንዲረዳቸውም ለዋቢነት የባህር ማዶ ፀሀፍትን ይጠቃቅሳሉ - ይህም ቢሆን ደግ፡፡

እውነት ነው፡፡ እዚህ ላይ ማንም ሊክደው የማይችለው ሀቅ አለ፡፡ ይኸውም ቀዝቃዛውን የዓለም ጦርነት መቋጨትን ተከትሎ የነፃው ፕሬስ በሁሉም አቅጣጫዎች ማበቡ እውነታ ነው፡፡ በዚህን ወቅት ብቅ ለማለት እድሉን ያገኘው ኢሕአዴግም የዚህ አካል መሆኑም እርግጥ ነው፡፡

ወታደራዊ አምባገነኑን የደርግ አገዛዝ መንኮታኮት ተከትሎ በኢትዮጵያ ታሪክ በቁጥር የበዙ የሕትመት ውጤቶችና የተለያዩ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ፖርቲዎች መፈጠራቸው ሌላው ሀቅ ነው፡፡ ለዚህም ኢሕአዴግ የፈጠረው ምቹ ሁኔታ መኖር ተጠቃሽ መሆኑ በአምደኞቹ ክህደት አለመላበሱ ያስመሰግናቸዋል፡፡

በደመ ነፍስም ቢሆን በኢትዮጵያ ለነፃ ፕሬስ ማበብና ለተቃዋሚ ፖርቲዎች መፈጠር በዋነኛነት ኢሕአዴግ ትልቁን ድርሻ መያዙን ሊጠቃቅሱ ሞክረዋል፤ ምንም እንኳን ለዚህ ሠናይ ተግባር ኢሕአዴግን በማወደስ ፈንታ ማንኳሰስ ቢቀናቸውም ግና እየጎመዘዛቸውም ቢሆን ሀቁን ጨርሶ ማድበስበስ አልተቻላቸውም፡፡

ያም ሆነ ይህ የፀሐፊዎቹ ዋነኛ ፍላጎት እውነተኛ ታሪክን ዳስሶ ለባለታሪኩ ሕዝብ ለመተው አይደለም፡፡ ይህን ከልባቸው ተነሳስተው ለማድረግ ብዙ ሲቸገሩ ተስተውሏል፡፡ ሀቁን ግልጥልጥ አድርጎ በማቅረብ ለሕዝብ ውሣኔ ዳኝነቱን ለመስጠትም አልፈቀዱም - አዋጭ የፖለቲካ ቁማር መስሎ ስላላገኙት ፀሐይ የሞቀውን እውነታ ላይ ላዩን ዳስሶ መሹለክለክን መርጠዋል፡፡

ሀቅን አፍርጥርጦ፤ እውነታን ዘክዝኮ ማቅረብ የህሊና ዳኝነትን ይጠይቃል፡፡ ይህ ግን በፀሐፊዎቹ ዘንድ የለም፡፡ ይብሱን የጋዜጠኝነት ሙያ ሥነ ምግባር በማይፈቅደው ሁኔታ የፖለቲካ ወገኝተኝነትን ተላብሰው የፈለጉትን መካብ፣ የጠሉትን ማንንጠጥና ማጠልሸት ሙያዬ ብለው ስለተያያዙት ብዙም አይደንቅም፡፡

አንድ እውነታ ግን አለ፡፡ ፀሐፊዎቹ ቢጎመዝዛቸውም ማንም እንደማይክደው ኢሕአዴግ በትረ ሥልጣኑን በያዘበት ወቅት በአገሪቱ በፈጠረው ምቹ ፖለቲካዊ፣

ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ አውዶች ምክንያት የፖለቲካ ፖርቲዎችም ይሁኑ ነፃው ኘሬስ እውን መሆናቸው ትልቁ ሀቅ ነው፡፡

የጋዜጠኝነት ሙያ ንድፈ ሀሳብ እንደሚያስረዳን ሙያው ሀቁንና ድብቁን ገላልጦ ለሕዝብ በማሳየት ሕዝቡ እውነታውን እንዲረዳ፣ የራሱን ሚዛናዊ ፍርድ እንዲሰጥ ማድረግ ማስቻል ነው፡፡ የጋዜጠኛው ተግባርም ሕዝብን ማስተማር፤ ማሣወቅና ማዝናናት ነው፡፡

ስህተቶች ሲከሰቱ እንዲታረሙ ጥቆማዎችን በመስጠት፣ በጎ ጎኖችን በማበረታታት የበለጠ እንዲጎለብቱ በሚል በሳል ሚዛናዊ ዘገባዎችን ማቅረብ ነው። ከዚህ ባለፈ ግን በፍፁም ጥላቻ ላይ የተመሠረተና ጨለምተኛና ፅንፈኛ አመለካከቶችን ብቻ የሚያራምድ ከሆነ ሕዝብን ከማደናበርና ከማሳሳት ውጪ ሙያዊ ኃላፊነቱን ተወጥቷል ማለት አይቻልም - በፀሐፊዎቹ የታየውም ይኸው ነው፡፡

የፀሐፊዎቹ ድምር ሀሳብና ፍላጎትም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ በፍፁም ጥላቻ ላይ የታጠረ ነው፡፡ እናም አጋፋሪዎቹ ሁሌም እንደሚያደርጉት ሕልማቸው ማኅበረሰብን ለበጎ ተግባር ማነቃነቅ፣ ትውልድን በመልካም ማረቅ ባለመሆኑ እውነቱን ሀሰት፣ ብርሀኑን ጨለማ፣ አድርገው ስለው ቢያቀርቡ አይገርም፤ አይደንቅ፡፡

ለያዙት ድብቅ አጀንዳ ማስፈጸሚያነት ያዋጣናል የሚሏቸውን የተንኮልና የምቀኝነት ሴራዎችን ሁሉ እየጎነጎኑ በዚያው መንገዳቸው ላይ ደንቃራ ሆነው ቢቆሙ አዲስ አይደለም፡፡

የሆነው ሆንና ቀዝቃዛውን የዓለም ጦርነት ማክተም ተከትሎ የተከሰቱ መንግሥታት መገለጫዎቻቸው የሆኑት የነፃ ኘሬስ ማበብና የተቃዋሚ ፖርቲዎች ማቆጥቆጥ የፅሑፉቸው ማጣፈጫ ያድርጓቸው እንጂ ውስጠ ነገሩ ማጠንጠኛው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ኘሬስ አልባ ነው ብሎ መሟገትና ለዚህም ያስረዱልናል የሚሏቸውን ሰበዞች እየመዘዙ የተለመደ ጥላሸት የመቀባባቱን ተግባር በመወሻከት ለመቀጠል ነው፡፡

እርግጥ ፀሐፊዎቹ ይዘዋቸው ከቆመሉት ዓላማቸው አንጻር ሲፈተሽ መግቢያው ላይ ብዕራቸውን በሌሎች እውነታዎችና ጨርሰው ሊደፈጠጡ በማይችሉ ሀቆች አሟሙቀና

የባህር ማዶ ተመራማሪ የሚሏቸውን አስረጂዎች አባሪ አድርገው ለማብራራት ይሞክራሉ፡፡

ይሁንና የፀሐፊዎቹ ድብቅ አቋምና የአስተሳሰብ ድምር ውጤት ሲቃኙ ወደ አንድ መደምደሚያ ያደርሱናል - በኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ የለም ወደ ሚል ጫፍ፡፡ ፀሐፊዎቹ ከፈለጉት መደምደሚያ ይድረሱ ሀቁ ግን ወዲህ ነው፡፡ የደርግ ውድቀትን ተከትሎ እስከ 1997ቱ ምርጫ ድረስ ነፃ ፕሬስና ተቃዋሚ ፖርቲዎች በአገሪቱ በብዛት ተፈጥረዋል - ይህም እውነት ነው፡፡ ነገር ግን ራሳቸው ባፈሯቸው ድክመቶችና ስህተቶች ተሽመድምደው ቀርተዋል፤ ራሳቸውን ጠልፈው ወድቀዋል - ይህም ሐቅ ነው፡፡

እዚህ ላይ ያለፈን ሀቅ ማድበስበስ ለማንም አይበጅም፡፡ ስለ እውነት…እውነቷ እንነጋገር ከተባለ ፀሐፊዎቹና በአስረጂነት የቀረቡት ባህር ማዶ “ተመራማሪዎች” እንደሚገልጹት ሳይሆን፤ ከሙያዊ ሥነ ምግባር ባፈነገጠ ሁኔታ የጋዜጠኝነት ተግባርን ሲከውኑ የከረሙት እኒያ የግል ፕሬስ ውጤቶች እና ጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፖርቲዎች ራሳቸው በነነነት ሴራና ተንኮል ተሸብበው መጥፊያቸውን አበጃጅተዋል፡፡ የራሳቸውን መጥፊያ የደጋገሱትና ያሰማመሩትም ቢሆኑ ራሳቸው ናቸው፡፡

በእርግጥ የጋዜጠኝነት ሙያም ሆነ የፖለቲካ ሥራ አስተዋይነትን፣ አርቆ አሳቢነትን ይሻሉ፤ ዝም ተብሎ ሥራ ስለታጣ ብቻ አዋጭነታቸው እየተፈተሸ ዘው ተብሎ የሚገባባቸው መስኮች አይደሉም፡፡ ኃላፊነትን ይጠይቃሉ፡፡

እንዳለመታደል ሆኖ ግን ለአብዛኛዎቹ የነፃ ፕሬስ ውጤቶች መክሰም ዋነኛ ምክንያት ተደርገው የሚቆጠሩት ራዕይ አልባነታቸው፣ ኪሳራ የመሸከም አቅማቸው አለመደንደኑ፣ የአስተዳደርና የሙያ ክህሎት ዝቅተኛነታቸው፣ ሙያቸውን ለሕዝብና ለአገር ወግነው አለመሥራታቸው እንደሆነ በግልጽ የታዩ እውነታዎች ናቸው፡፡

እስቲ ወደ ኋላ ጥቂት ጊዜያትን እንመለስ፡፡ በነዚያ ወቅቶች በነፃ ሚዲያ እና በጋዜጠኝነት ስም ምን ምን ተግባራት ሲከወኑ ቀዩ? እነዚህ ጉዳዮች ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጥንቃቄ ይከታተለው የነበረ ጉዳይ ነውና ያውቀዋል፡፡

ጥቂት የማይባሉት የግል ኘሬስ ውጤቶች ይዘዋቸው በሚወጧቸው ግልጽና ከባህላችን ባፈነገጡ ልቅ የወሲብ ማስተማሪያ ዘገባዎቻቸው የሕዝብ ተቃውሞ ገጥሟቸው ከገበያ ተሽቀንጥረው የወጡ መኖራቸውንም እናስታውስ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ያገኟቸውን ሠላም ጠብቀው፣ ልማታቸውን እያፋጠኑ በዴሞክራሲያዊ አንድነት ትስስር መኖር እንዳይችሉ ለሌላ ግጭት ሲቀሰቅሱ፣ ዜጎችን እርስ በርስ በማላተም ጦር ለማሳበቅ ሲያነሳሱ የሰነበቱ የግል ፕሬስ ውጤቶች ለውድቀታቸው ከራሳቸው በላይ ማንን ተጠያቂ ሊያደርጉ እንደሚያመኙ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡

ይህ ብቻ ሳይሆን ዜጋውን ለሌላ ዙር ፍልሚያ ሲያዘጋጁት እንደነበር የሚጠፋን አይደለም፡፡ ይህንን የቅርብ ጊዜ ትዝታን መካድ አይገባም፤ ይህን ያገጠጠ እውነት ሸፋፍኖ ማለፍም ያስተዛዝብ ካልሆነ በቀር ትርፍ አያስገኝም፡፡

ኢትዮጵያዊያን ለዘመናት በአብሮነት ተሳስረን የኖርን ሕዝቦች ነን፡፡ ባህላችንም፣ እምነታችንም የሚሰበከው በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነትንና መቻቻልን ነው፡፡ ታዲያ የወቅቱ ነፃ ኘሬስ ተብዬዎች ያኔ በዘመቻ መልክ በሚመስል ሁኔታ ተሰነዳድተው የተነሱት ይህን አብሮነታችንን የሚንድና እርስ በርሳችን የሚያብላላ የጥፋት አውድማ መፍጠርን ነበር - አልተሳካላቸውም እንጂ፡፡

ፀሐፊዎቹ የሚሞግቱላቸው ነፃ ኘሬሶች አብዛኛዎቹ በእንዲህ መሰል የሁከት ተግባራት ተሰማርተው የነበሩ በውጤታቸውም ሕዝብና መንግሥት አሽቀንጥረው የተፏቸው፤ የእውቀትም ሆነ የሥነ ምግባር ችግር የነበረባቸው አውታታዎች ነበሩ፡፡

ሀገርን በአንድ ለሊት ለማጥፋት በሚመስል ሁኔታ በነጻ ፕሬስ ስም ተደራጅተው ሴራ እንዲጎነጉኑ ያሻቸውን ይፈጽሙ ዘንድ መፍቀድ የዜጎችን ደህንነትና የአገርን ሠላም እንዲጠብቅ አደራ የተሰጠው መንግሥት በቸልታ ያልፋል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው፡፡

በተለያዩ ሚዲያዎች ውስጥ ተሸሽገው ያንን ታላቅ የጋዜጠኝነት ሙያ መለያን ደርበው ሕዝብን ለማበጣበጥና አገርን ለማመስ ቆርጠው የተነሳሱ ጥቂቶችን መንግሥት

ሥርዓት ማስያዝ የተሰጠው ኃላፊነት ጭምር ነው፡፡ ይህን መከወን ደግሞ ኃላፊነትን የመወጣት ግዴታውም ጭምር ነው፡፡ መንግሥት በወቅቱ መወሰድ ያለበትን እርምጃ ሳይወስድ ቀርቶ፤ የከፋ ችግር ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ ተጠያቂው ማን ይሆን ነበር? ይህም መዘንጋት የለበትም፡፡

ጉዳዩን ወደ ማጠቃለሉ ስንመጣ የአብዛኛዎቹ የሕትመት ውጤቶች በወቅቱ የሚያሰፍሯቸው ዘገባዎች ጭብጥ ሲመዘን ውጤቱ ያው ጥፋት እንደነበር ያስማማናል፤ ዛሬም በዚያው ቅኝት የተሞሉ አንዳንድ የህትመት ውጤቶች በየጊዜው የአመፅ ጥሪን የሚያስተጋቡ የጥፋት መልዕክተኝነታቸውን አልሳቱም - በዚያው መሥመራቸው ላይ ቆመው ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ደንቃራ ጉዞዎችን ወጥቶ፤ ወርዷል ይላሉ እነዚሁ ፀሐፊዎች፡፡ ፕሬሱ አስቸጋሪ መንገዶችን እንዳቋረጠ የሚነግሩን ፀሐፊዎቹ የባህር ማዶ አጥኚዎች ከሚሏቸው አስረጂዎቹ ባገኟቸው የምርምር ምልከታዎች በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡

የሀገሪቱ የፕሬስ ነጻነት የሚገኝበት ሁኔታን ለመዳሰስ፣ ያጋጠሙትን ችግሮች ለመፈተሽ፣ የሚጠበቅበትን ተግባር በአግባቡ እንዳይከውን ጋሬጣ የሆኑበትን ምክንያቶች ለመቃኘት ከእኛ በላይ ቅርቡ ማን ይሆን? የግድ ባህር ማዶዎቹ እንዲህ ነው የሚሉንን እየተቀባበልን ሁኔታዎችን መፈተሽና መመዘን ለምን አስፈልጎ ይሆን?

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ እድገት ይሁን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ረዥም ጉዞን ያላለፈ፣ ለጋ እድሜ ላይ የሚገኝ ከመሆኑ አንጻር ክፍተቶች ሊኖሩበት እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ከእንከን የነፃና የፀዳ አድርጎ መከራከር ግን አይቻልም፡፡

የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን በቅርቡ የጀመረች አገር ይቅርና ከሁለት መቶ ዓመታት ዕድሜ በላይ እንዳስቆጠሩ የሚነገርላቸው የበለፀጉ አገራትም ቢሆኑ፤ ፍፁም የበቃን ነን አይሉም፡፡ የበቃለት ዴሞክራሲና ፍፁም ነፃ ፕሬስም አልገነቡምና፡፡

ከዚህም ጋር በዚህ ሂደት ውስጥ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ክፍተት መኖሩ አይቀርም። ምንም እንኳን የግድ ችግር ይከሰት ባይባልም ገና ወፌ ቆመች ዳዴ እያለች ባለች

አገር የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታው ውስጥ እንከን አይጠፋም ብሎ መከራከር የዋህነት ነው፡፡

በፈርጀ ብዙ የስም ማጥፋት ዘመቻ እየተነሳሱ የአገራችንን ገፅታና የሕዝባችንን አብሮነት የሚሸረሽሩ ተራ አሉባልታዎችን መንዛት አግባብ አለመሆኑ ያግባባናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ለምን ቢባል ጋዜጠኝነት ሙያም ቢሆን የአገርን ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስቀድም የሥራ ዘርፍ ነውና፡፡ እናም "ጋዜጠኞቻችን" ሕዝቦቻቸውን ለኒዮ ሊብራሊስቶች በሚመች መልኩ ብዕራቸውን አሹለውና ምላሳቸውን ስለው ለእኩይ ምግባር ሲራኮቱ ማስተዋል ያሳዝናል፤ ያስተዛዝባል፡፡ እርግጥ በተጨባጭ እንደተረጋገጠው ጥቂት የማይባሉ የፕሬስ ሰዎች ለምዕራባዊያን አገልጋይ ሆነው ተሰልፈው እስከመሸለም ደርሰው ነበር፤ ዛሬም ቢሆን የሚታጩ የጠፉ አይመስለኝም፡፡ በጥቅማ ጥቅም እየተደለሉ ሕዝብን ከመሸጥና አገርን ከመለወጥ ወደኋላ እንደማይሉም ቀደምት ተግባራቸው ምስክር ነው፡፡

ምን ይህ ብቻ፡፡ የሌላውን ሃሣብና አመለካከት በብዕር ከመሞገት ይልቅ የተከራካሪውን ስብዕና ማለትም ብሔሩን፣ ኃይማኖቱን፣ ቋንቋውን እየጠቃቀሱ በማንቋሸሽና ስም በማጥፋት፣ የዜጐችን ማንነት በማዋረድና በማጥላላት ላይ ጊዜያቸውን የሚያጠፉ አንዳንድ የግል ፕሬሶች አቆጥቁጠው እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

ቁጥራቸው እንደ ያኔው አይብዛ እንጂ ዛሬም ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። ከፊሎቹ ሕዝቡ ራሱ አንቅሮ ስለተፋቸው፤ ከፊሎቹ ደግሞ መንግሥት አጥፊ አካሄዳቸውን ተገንዝቦ በወቅቱ ሥርዓት ስላስያዛቸው አሊያም ኪሳራ መሸከም ተስኗቸው ከጨዋታው ውጪ ሆነዋል፡፡

እዚህ ላይ አንድ ቁምነገር ማስተዋል ተገቢ ይሆናል፡፡ ጋዜጣን የፅንፈኞችና የአሸባሪዎች አስተሳሰብ ማራመጃ በማድረግ ህገ መንግሥቱንና ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በአመፅ ለመናድ መቀስቀሻ ማድረግ ከቶ እንደማይቻል የጋራ መግባቢያ ልንይዝ ይገባል፡፡

ፀሐፊዎቹ እንደሚያትቱት መንግሥት በነፃው ፕሬስ ስም የተሸፈኑ ወንጀለኛ ጋዜጠኞችን ለምን መረን አልለቀቃቸውም? የሚሉ ከሆነ ይህ የሚያነጋግር ጉዳይ

ነው፡፡ አመጽንና ሁከትን የሚሰብኩ እንዲሁም እርስ በርሳቸው እንደ እፉኝት ተበላሉ እያሉ የሚያነሳስ የጥፋት ተስፈኞችን አይቶ እንዳላዩ ማለፍ ከአንድ ኃላፊነትና ሰብዓዊነት ከሚሰማው መንግሥት አይጠበቅም። መንግሥት ሽብርን የሚነዙ የአሸባሪ ተባባሪዎችን በህግ ተጠያቂ ማድረጉ ሥራውም፣ መብቱም፣ ግዴታውም፣ ኃላፊነቱም ጭምር መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ይህን በማድረጉም የፕሬስ አፈና ተደርጐ መወሰድ አይገባም፡፡

ነባራዊው ዓለም ሆነ የጋዜጠኝነት ሙያ የሚያስረዳን ነጥብ ነፃ ፕሬስ ነፃ ውንብድና ወይም ነፃ ሽፍትነት አለመሆኑን ነው፡፡ ነፃ ፕሬስ የግል ፍላጐታችን የበላይነት እንድንቀዳጅ ስንል ብቻ የሌለን ነገር በመፍጠርና ውሸትን በመፈብረክ፣ ከፍ ሲልም የሌሎችን መብትና ሉዓላዊነት ኢ ሥነ ምግባራዊ በሆነ መንገድ የምንገፋበትና የምንነግድበት ሽቀጥም አይደለም፡፡

ለፀሐፊዎቹ ግን ነፃ ፕሬስ ማለት እንዲያ መሆኑ ነው። ሽሪኮቻቸው ጭምር ሽሽግ ዓላማዎቻቸውን የሚያሳካላቸውን ምቹ አውድ እስካላገኙ ድረስ ነፃ ፕሬስ በእነሱ ዕይታ ነፃ ፕሬስ አይደለም። በእነርሱ የተወላገደ ሽውራራ እይታ የነፃ ፕሬስ ትግል እውን የሚሆነው ጥፋት ሲመዘገብ ብቻ መሆኑ ይሆን እንዴ?...

ጤነኛ አዕምሮ ያለው ዜጋ እንደሚረዳው ልማታዊ ጋዜጠኝነት በዴሞክራሲ ባልዳበሩ ሕዝቦችና መንግሥታት ዘንድ ቁልፍ የብልጽግና መሣሪያ እንደሆነ ነው፡፡ አመለካከቱ ሕዝቦችን ለልማት ለማነሳሳትና የብልጽግና ከፍተኛው ማማ ላይ እንዲወጡ ማስቻል ነው። በየትኛውም ዓለም የሚሰራበት የንቅናቄ መሣሪያም ይኸው ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የሕዝቦች አብሮነት የሚጠብቅበትን፣ የዴሞክራሲ ባህል ግንባታ የሚዳብርበትን እንዲሁም የመተሳሰብና የጋራ ልዕልና የሚሰፍንበትን ቀመር ይሰብካል፤ በዚህ ዓላማና ዙሪያ ተንቀሳቅሶ ይሰራል፡፡ ይህ እሳቤ ዛሬ በለፀጉ በምንላቸው አገራት ሣይቀር የታለፈበት ጎዳና ነው፡፡

በአንድ ጀንበር የተነገባ የዴሞክራሲ ሥርዓትም ይሁን የፕሬስ ነፃነት አስተሳሰብ መቼም ኖሮ አያውቅም፡፡ በመሆኑም ችግሮች መኖራቸው የግድ ነው ባይባልም፤ በሥራ ሂደት እንከኖች ባጋጠሙ ቁጥር የተሰማሩበትን የፖለቲካ ነውጠኝነት እውን

ለማድረግ በአሥር ሺህዎች አባዝቶ ነገሮችን ለማወሳሰብና ሕዝብና መንግሥትን ለማምታታት የሚደረግ ሴራ ግን አግባብነት እንደሌለው ነገሮ ማለፍ ተገቢነት እንዳለው መጠቆሙ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

የነፃ ኘሬስና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ህግና ሥርዓት ከሚፈቅደው ውጭ አፈንግጦ መረን በመውጣት ያልተገባ ጥቅም ለማግበስበስ በማሰብ ብቻ ከንቱ መሯሯጥ ተገቢ አይደለም።

በልማትና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መካከል ፍፁም የማይፈታ ዝምድና በመኖሩ ልማትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የሚያስታርቅና ሁሉን እውነታዎች አግባብቶና አጣጥሞ የሚያራምድ የኘሬስ ፍልስፍና ማቋቋምና ምቹ አውድን መፍጠር ከማንኛውም ሕዝባዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግሥት የሚጠበቅ ቁልፍ ተግባር መሆኑም መዘንጋት የለበትም፡፡

ይህ ሲባል ግን ልማትንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማስፈን ኘሬስ መታፈን አለበት ማለት አይደለም፡፡ በአገራችንም “ወንጀለኛ ጋዜጠኛ” እንጂ ነፃ ኘሬስ የታፈነ ባለመሆኑ ጉዳዩ ብዙ የሚያሟግት አይደለም። ለነገሩ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ተነግሯል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ በሽብር ተግባር በመሰማራት እንጂ በፃፈው ፅሑፍ የታሰረ ጋዜጠኛ የለም፡፡ ይህም ከኘሬስ አፈና ጋር በየትኛውም መስፈርት የሚተሳሰር አይደለም፡፡

በአንፃሩም ህገ ወጥ ዘገባዎችን የጥፋት ድርሣናትን አድርጎ በማቀጣጠል ዜጐችን ለማብላላት ዘወትር የሚወተረተሩ ግለሰቦች ተጠያቂ መሆናቸው እንደ ኘሬስ አፈና መቆጠር የለበትም - ጉዳዩ የህግ የበላይነትን ማስከበር ነውና።

ጥቂት የማይባሉት ሴን የተባሉ ፀሀፊን ጠቅሰው እንደሚያትቱት የዴሞክራሲ ባህል የሚገነባው በነፃ ኘሬስ ላይ በሚደረጉ ሕዝባዊ ክርክሮች አማካይነት ነው ይላሉ፡፡ ይህ ሀቅ ነው። ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መቀላጠፍ የግድ ተደርጐ የሚጠቀሰው የአደባባይ ውይይትና በምክንያታዊነት ላይ የተመሠረተ የሀሣብ ፍጭት መሆኑ አያከራክርም፡፡

ዜጎች በነፃነት ሲወያዩ፣ ሀሣብ ለሀሣብ ሲሟገቱ፣ ለልማት የሚበጁና ዴሞክራሲውን የሚያራምዱ የአስተሳሰብ ብልጭታዎች ሲፈልቁ፤ ዳብረው ለልማት ሊውሉ ይችላሉና፡፡ አንዳንድ ጋዜጠኛ ተብዬዎች በነፃ ኘሬስ ስም የፖለቲካ ንግድን ለማጧጧፍ ሲራኮቱ በሚታይበት አገር ውስጥ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ማለም አጋጣሚውን ለፅንፈኞች መፈንጫ መፍቀድ ከመሆን የዘለለ ፋይዳ የለውም፡፡ እናም ፀሐፊዎቹ ኢሕአዴግን እያብጠለጠሉ በመጻፋቸው አይታሰሩም፡፡ አልታሰሩምም፡፡

እዚህ ላይ በድጋሚ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ማንንም ግለሰብ የሚያሳስረው ተጠያቂ የሚያደርገው መፃፍ ሳይሆን ወንጀል መሥራቱ ነው፡፡ የየትኛውም አገር ፕሬስ በአገሩ የህግ ማዕቀፍ ውስጥ የሚሰራ እንደመሆኑ መጠን፤ በነፃ ኘሬስ ስም ጥፋትን መስበክ ያስጠይቃል፤ ያስቀጣል ጭምር፡፡

ፀሃፊዎቹ ኢሕአዴግ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ኘሬስን ከአደባባይ ለማራቅ ጠንክሮ ከመሥራቱ ባሻገር ሁለት ህጎችን እንዳፀደቀ ይጽፋሉ፤ የኘሬስ አዋጁን እንደ አብነት በመጥቀስ፡፡ እርግጥ መንግሥት የኘሬስ አዋጅ ማውጣቱ አይካድም።

ይሁን እንጂ የኘሬስ አዋጅ የወጣው ኘሬስን ከአደባባይ ለማራቅ ሳይሆን ሥርዓትን ተከትሎ የአገሪቱን ልማትና ዴሞክራሲ የሚያሳለጥንበት ምቹ አውድ ለመፍጠር ታልሞ የወጣ ነው፡፡

ማንኛውም ጋዜጠኛ ከየትኛውም የመንግሥት አካል በቂ መረጃ እንዲያገኝ፣ የመንግሥት አካልም መረጃ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ነው። ለነገሩ የኘሬስ አዋጅ ህግ ማውጣት በኢትዮጵያ አልተጀመረም፡፡

በየትኛውም ዓለም ነፃ ኘሬሱን ፈር ለማስያዝ የሚያስችል ደንቦችና የህግ ማዕቀፎች ይቀረፃሉ። እናም የህጉን መውጣት በዓይነ ቁራኛ ማየቱ ስህተት ነው። ያለአንዳች ህግ እንደፈለግነው እንሆናለን ለማለት ካልፈለገ በስተቀር።

ይህ ግን የሚሆን አይደለም። ፕሬስ ከህግ ማዕቀፍ ውጪ ሆኖ ሲሰራ በሩዋንዳ፤ በቅርቡም እንደ ኬንያ ባሉት አገራት ውስጥ ያስከተለውን እልቂት መዘንጋት አይኖርብንም።

ሚዲያው ነፃና ጤናማ ሆኖ እንዲሰራ የተቀረፀን አዋጅ በደፈናው ማጥላላት ከተጠያቂነት ለመራቅ የታለመ በመሆኑ በየትኛውም መሥፈርት ተቀባይነት አያገኝም፡፡ ሀገርን ለመናድና አብሮነታችንን ለማመስ የሚጣደፍ አጥፊ፣ የፀረ ኢትዮጵያ አቀንቃኝ ኃይሎች ጉዳይ አስፈጻሚዎችን ሕጉና ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት ተጠያቂ ማድረግ ከኘሬስ አፈና ጋር የሚተሳሰርበት አሊያም የሚቆራኝበት አንዳችም ምክንያት የለም፡፡

ጋዜጠኛም ይሁን የሌላ ሙያ ባለቤት ሕግን እስከተላለፈ ድረስ መጠየቁ የግድ ነው፡፡ በየትኛውም አገር ውስጥ እንደሚደረገው ሁሉ በኢትዮጵያም የሕግ የላይነት መረጋገጥ አለበትና።